በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ. 251859

ታህሳስ 29 ቀን 2016 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንዳሻው አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

ዋዚሞ ዋሲራ

ሰናይት አድነው

**አመልካች፡-** መ/ር ሐዋዝ አባዲ ወንድም

**ተጠሪ፡-** ደቡብ ትግራይ ሃገረ ስብከት

አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ እንዲሁም አጣሪ ችሎቱ መዝገቡን ለሰበር ችሎት የመራበት ትዕዛዝ ተመርምሮ ተከታዩ ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው አመልካች በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ደቡባዊ ዞን ማይጨው ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 50/2015192 በቀን 05/07/2015 ዓ.ም የሰጠውን ብይን እንዲሁም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 270/15 በቀን 05/08/2015 ዓ.ም እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪ ችሎት በመ/ቁ. 01/2015/1354 በቀን 18/09/2015 ዓ.ም ያሳለፉትን ትዕዛዝ በመቃወም ነው፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው አመልካቾ በስር ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ በቀን 14/09/2011 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ የደቡብ ትግራይ ሃገረ ስብከት ጊዜያዊ ስራ አስኪያጅ ሆኜ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

እንድሰራ፤ በኋላም በቀን 11/06/2012 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ዋና ስራ አስኪያጅ ሆኜ እንድሰራ ተመድቤ በመስራት ላይ እያለሁ ከ1988 ዓ.ም ጀምሮ በስራ ላይ ካለው የቤተ-ክርስቲያኒቱ ሰራተኞች መተዳደሪያ ደንብ ውጪ ከስራ መደቤ ላይ ተነስቼ ወደ ሊቃውንት ጉባኤ ሰብሳቢ የስራ መደብ ላይ እንድሰራ የተዘዋወርኩ ስለመሆኔ በቀን 10/05/2015 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ የተገለፀልኝ በመሆኑ በአሰሪና ሰራተኛ ህጉ መሰረት ያልተከፈለኝ ደሞዝ እና ጥቅማ ጥቅም ተከፍሎኝ ወደ ቀድሞው የስራ መደቤ እንድመለስ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ በሰጠው መልስ አመልካች ያቀረቡት ክስ ከመንፈሳዊ አገልግሎት ጋር በተገናኘ ጉዳይ ላይ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ አከራክሮ የመወሰን ስልጣን የለውም የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማቅረብ ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ካደመጠ በኋላ አመልካች በጉዳዩ ላይ ያላቸውን ቅሬታ በአስተዳደራዊ መንገድ አቅርበው መፍትሔ ሳይጠቁ በቀጥታ ለፍርድ ቤት ክስ ማቅረባቸው ተገቢነት የለውም በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ ይግባኝ እና የሰበር አቤቱታ የቀረበላቸው የበላይ ፍርድ ቤቶች ቅሬታውን ውደቅ አድርገዋል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው፡፡ አመልካች ነሀሴ 3/2015 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር ማመልከቻ ተፈፀመ የሚሉትን ስህተት ዘርዝረው የስር ፍርድ ቤቶች ያሳለፉት ውሳኔ ተሽሮ ጉዳዩ ታይቶ እንዲወሰን በነጥብ ወደ ስር ፍርድ ቤት እንዲመለስ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

እንደሚታወቀው በኢፌዲሪ ህገ-መንግስት አንቀጽ 80(3) እና በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 እንደተመለከተው ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ስልጣን መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበትን የመጨረሻ ውሳኔ ማረም ነው፡፡ መሠረታዊ የህግ ስህተት ሲባል ምን ማለት እንደሆነ ደግሞ በአዋጁ አንቀጽ 2(4) ስር ተዘርዝሯል፡፡

በሌላ በኩል መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል የተባለውን የመጨረሻ ውሳኔ የሰጠው የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ከሆነ ጉዳዩ ለፈደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ሊቀርብ የሚችለው ውሳኔው ህገ-መንግስቱን ወይም ይህ ሰበር ችሎት አስቀድሞ የሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሚቃረን ሲሆን ወይም አግባብነት የሌለውን ህግ በመጥቀስ ወይም ህግን ያለአግባብ በመተርጎም የተሰጠ ሆኖ ጉዳዩም ለህዝብ ጥቅም ሀገራዊ ፋይዳ ያለው ብቻ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 10(1)(ሀ) እና (መ) ስር በግልጽ ተመላክቷል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ከዚህም ሌላ በኃይማኖት ተቋማት ውስጥ መንፈሳዊ/ኃይማኖታዊ አገልግሎት የሚሰጥ ሰራተኛ ከተቋሙ ጋር ያለው የስራ ግንኙነት በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ የሚሸፈን ስላለመሆኑ እና በዚህም ምክንያት ፍርድ ቤቶችን ጨምሮ የስራ ክርክር ጉዳዮችን በሚመለከቱ ተቋማት ሊስተናገድ የሚችል ስላለመሆኑ ይኸው ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ/ 18419፤ 60999 እና በሌሎችም ተመሳሳይ መዛግብት አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ እነዚህ የሰበር ውሳኔዎች በተያዘው ጉዳይም በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 ዓ.ም አንቀፅ 10 መሰረት በተመሳሳይ ተፈፃሚነት አላቸው፡፡

በተያዘውም ጉዳይ አመልካች በአሰሪና ሰራተኛ ህጉ መሰረት አዲስ የተመደብኩበት ሊቃውንት ጉባኤ ሰብሳቢ የስራ መደብ ቀርቶ ያልተከፈለኝ ደሞዝ እና ጥቅማ ጥቅም ተከፍሎኝ ወደ ቀድሞው የስራ መደቤ ማለትም የደቡብ ትግራይ ሃገረ ስብከት አስኪያጅነት እንድመለስ ይወሰንልኝ በማለት ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ የሚሸፈን ባለመሆኑ እና በዚህም ምክንያት ፍርድ ቤቶችን ጨምሮ የስራ ክርክር ጉዳዮችን በሚመለከቱ ተቋማት ሊስተናገድ የሚችል ባለመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ያሳለፉት ብይንና ትዕዛዝ በውጤቱ የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በመሆኑም በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 28(2) እና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ስርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 7(1) መሰረት አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ውድቅ ተደርጓል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፅ/ወ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !